12 ተኛ ክፍል matrick የወሰዳችሁ

እንኳን ደስ አላችሁ በመፈተናችሁ

እንግዲህ ቻሉት ውጤቱን መጠበቅ

በደንብ ተዝናኑበት አሁን ባለው ክረምት

አያድርገውና ውጤት ባይመጣልህ

አተክዝ አታስብ ሌላ መልካም አለ አለህ ያዘጋጀልህ

ደሞ በሌላ በኩል ውጤት አምጥታችሁ ግቢ ለምትገቡ

ትንሽ ምክር ብጤ ጣል ላርግላችሁ

ከናንተ የማልሻል እኔ ወንድማችሁ

ዩኒቨርሲቲ ማለት ትንሽ ሀገር ናት

ሙስሊም ክርስትያኑ የሚገኝበት

አማራ ኦሮሞ ስልጤጉራጌ ሚዋሀድበት

ስለዚህ ወንድም እህቶቼ ብልሀት ያስፈልጋል

በዝች ትንሽ ሀገር ለመኖር በመቻቻል

ቦታው ይፋ ከሆነ የተመደባችሁበት

ስለጊቢው አጥኑ በቻላችሁት ፍጥነት

የምትገቡ ጊዜ እንዳይዛችሁ ፍርሀት

ታዲያ አለህ ፈቅዶ ግቢ ገብታችሁ ዶርም ከያዛችሁ

ሰላም ተባባሉ ከዶርም ሜታችሁ

ስለማይቀር ዶርም ውስጥ ውጤት መጠያየቅ

ጥሩ ውጤት ያላችሁ ውጤታችሁን ደበቅ

የአደም ልጅ ፀባይ ስለማይታወቅ

ደሞም ስለሚኖር ቅናት ምቀኝነት

★★★★

ክላስ ከጀመረ ትኩረት ያስፈልጋል

መፎረፍ ሚስ ማድረግ በጣሙን ይጎዳል

ፈተና ካመለጠ ዋጋ ያስከፍላል

ይህንን ምላችሁ ለአንድ ምክንያት ነው

የ ***freshman*** ውጤት እጅጉን ወሳኝ ነው

የመስክ መለያ አንዱ መስፈርት ነው

★★★★

ጥሩ ውጤት ለመስራት የሚያስፈልጋችሁ

በደንብ ማንበብ ነው ***focus*** አድርጋችሁ

ማንበብ ማጥናት ብቻ ስለማይበቃችሁ

ወደ ኻሊቃችን ዱዓ እያረጋችሁ

በ አምስት አውቃት ሰላት እየበረታችሁ

ዲናችሁ ላይማ እንዳትዘጉ

መቼ ተጎዱና አለህን የያዙ

ይልቁንስ ብዙ እልፉን አተረፉ

★★★★

High school ሳላችሁ ያስለመዳችሁትን

አስቀጥሉት እዛም የማንበብ ሙዳችሁን

የአረህማን ስራ እኔ ይገርመኛል

የሰውን ልጅ ለያይቶ ፈጥሮታል

አንድአንዱ ቀን ሙሉ አንብቦ አንብቦ አንብቦ

መፅሀፍ አገላብጦ ምሳሌውን ሰርቶ የተረዳውን

ደሞ ሌለው ይረዳዋል ትንሽ አንብቦት

አይጠፉም*(2x)*አንድአንዶች ቀኑን ሙሉ አንብበው

ማታም የሚያነቡ እንቅልፋቸውን ትተው

እነሱን አይታችሁ ***tension*** እንዳትሆኑ

ሌለ አትመልከቱ እራሳችሁን ሁኑ

ትምህርት በ ተፈጥሮ አይፈልግም ***tension***

መታገል ነው እንጂ ልክ እንደ ***friction***

በነገራችን ላይ ማን እንደ ***Freshman***

ከሱ አንፃር እንደውም ***High school*** ይከብዳል

እንዳትዘናጉ ይሀንን ስላችሁ

ካጠናችሁ ብቻ ነው የሚቀላችሁ

★★★★

አንድም ሁለት ሺ ከሚለክለችሁ

አባካኝ አትሁኑ እየቆጠባችሁ

በዛውም ቁጠባን እየተማራችሁ

የተላከልህን በሳምንት ጨርሰህ

የት ትሄዳለህ የትስ ትገባለህ

ማንበብ ማጥናት ትተህ ዶርም ትተኛለህ

★★★★

Assignment ፈተና በደንብ መስራት ነው

አንድም ሁለት ማርክ ትልቅ ዋጋ አለው

አንድአንዴ *1* ማርክ ከ *5* እኩል ነው

ይህንን ምታውቁት *grade* ሲሰራ ነው

✍✍✍✍✍✍

ኢ/ማሊክ ኑረዲን

2016